# ከእነ ለማ ከዚህ በላይ ምን ያድርጉ? ሸክም ከምንሆን የሕዝቡን ትግል እንርዳ! ካልሆነ ዝም! (ሰርፀ ደስታ – የሳተናው አምደኛ)

March 10, 2018



የሰሞኑ ወሬ ለእነ ለማ አሳቢ በመምሰል የሕዝብን ትግል ለወያኔ እጅ መልሶ ለማስገባት የሚፍጨረጨሩ የበዙበት ይመስላል፡፡ ወያኔ በይፋ ጸረ-ሕዝብ አዋጅ አውጥታ ሰው እየፈጀች በአለችበት በዚህ ወቅት አዋጁን ሁሉንም ይቃወመኛል ብላ የምታስበውን ለማጥፋት ልትጠቀምበት እንደሆነ መቼም እንግዳ ነገር ሆኖ አይመስለኝም፡፡ ሰሞኑን አቢኤን መረጃ አያወጣም፣ ለማም ሆነ ሌሎች ለሕዝብ እየተናገሩ አደለም ሌላም ሌላም ወሬ በዝቷል፡፡ እነ ለማ እኮ ያሉት ግልጽ የሆነ ጦርነት ላይ እንጅ አሜሪካና ሌላ አገር ፌስቡክ ላይ የማሰለውን ለመቀባጠር ጊዜና እድል እንዳለው አደለም፡፡ በየአገሩ በነጻነት መናገር የሚችለው አፉ ተለጉሞና የወያኔን ፕሮፓጋንዳ የሚነዛ ሌላ ሸክም ሆኖ እያየን ግልጽ ጦርነት ውስጥ ያሉትን ሁሉን ነገር ይናገሩ ማለት አላማው ምን ይሆን? እነለማ ከመቼውም ጊዜ እየታገሉና ትግላቸውም እየተሳካ መጥቷል፡፡በስካሁን የእነለማ ቡድን የወሮበላውን ሴራ አደባባይ አውጥቷል፣ የሕዝብ ለሕዝብ አንድነትን ፈጥሯል፣ የወያኔን ሥር የሚነቅል መሠረት መስርቷል፣ በሺዎች የሚቆጠሩ በማሰቃያ የታጎሩ ወገኖችን አስፈትቷል፣ ከሕዝብ ጎን ሊቆሙ የሚችሉ የሕዝብ ተወካዮችን አፍርቷል፣ ለአገርና ሕዝብ ወግነው የሚቃወሙ (ነገሩ እንድ ብቻ ሆኖ ተገኘ እንጂ) ቡድኖችን በይፋ በኢትዮጵያ ፖለቲካ እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርቧል (ጥሪውን የተቀበለው ግን ኦፌኮ ብቻ ነው)፣ ወሮበሎች ገፍተው የጣሏቸውን የአገሪቱ ፕሬዘደንት የነበቱትን እንደመንግስት ሙሉ መብታቸው እንዲጠበቅ አድርጓል፣ በመጨረሻም በሕዝብ ላይ የታወጀውን የሽብር አዋጅ በመቃወም በፓርላማ ውድቅ አድርጓል፣ አሁንም እየታገለ ይገኛል፡፡

ለመሆኑ የለማ ቡድን ጸረ-ሕዝብ አዋጁን ውድቅ አድርጎት እያየን በአለም አቅፍ ደረጃና ይህንንም አስመልክቶ በየዓለማቱ የሚኖረው ዲያስፖራ ተብዬው መቼ ለዓለም ይህን የወሮበላ ድርጊት ሊያሳይ ተጽኖ ፈጣሪና ሊታይ የሚችል ሰላማዊ ሰልፍ እንኳን አደረገ፡፡ እነ ላማ ምን እንዲያደርጉ ነው የሚጠበቀው? ከዚህስ በላይ ምን ያድርጉ? ማድረግ ከሚገባቸው በላይ እያደረጉም ነው! ለመሆኑ እነሱን ይህን ማድረግ አለባቸው ይህን ማድረግ የለባቸውም  የምትሉ እናንተ እንማን ናችሁ? በግልጽ ከሕዝብ ጎን እንደቆመና ትግላቸውንም በአግባቡና በሰላማዊ መንገድ በፍጥነትም እያካሄዱ ናቸው፡፡ እስካሁንም ብዙ ድል ተጎናጽፈዋል፡፡ እስኪ ከሌላ ወገን ትንሽ እንኳን አስተዋጽዖ ያረገ ማን ነው? ከተቃዋሚስ ማን ነው ሌላው ይቅርና መግለጫ በማውጣት ይሄን የሽብር-አዋጁን እንኳን የተቃወመ ሕዝብንስ ማስተባበር የሞከረ? አንድ ያየነው ድሮም በቁርጠኞች እንደሚመራ የምናውቀው ከኦፌኮ በቀር እስኪ አንድ እንኳን ጠቁሙ፡፡ እነለማ ወያኔን

ከሕዝባቸው ጋር ወደመቃብር እንደሚያወርዱት አሁን ያለው እውነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ በዛው ልክ ጠላትም ላለመሞት የሞት ሽረት እያደረገ ነው፡፡ አዋጁን በይፋ የለማ ቡድን ጥሎታል፡፡ አሁን እየሆነ ያለው ለ 27 ዓመት ራሱን ሲያደራጅ የኖረው ወንበዴ ቡድን በይፋ ጦርነት የከፈተበት ነው፡፡ መከላከያውን፣ ደህንነቱን፣ ፌደራል መዋቅሩን ሁሉ በራሱ ሥር ሲያደርግ የኖረው የወሮበላ ቡድን አሁን እየተጠቀመ ነው፡፡ አሁን ሰላማዊ ሕጋዊ ምናምን የሚባል ነገር አይሰራም፡፡ እነ ለማ እስካሁን የሄዱበት ሕጋዊ ሒደት ነው፡፡ አንዳንዶችማ የሚናገሩትንም የሚያስተውሉት አይመስለኝም ለማ ሕጋዊ ሥልጣኑን ተጠቅሞ፣ ኦሕዴድ እንዲሕ ማድረግ አለበት እንዲ ማድረግ የለበትም ስንል ስለምን እንደምናወራ እንኳን አናስብም፡፡ በአጭሩ ሕግ የሚባል ነገር ከማያውቅ 27 ዓመት ለውንብድና ሲዘጋጅ ከኖረ ቡድን ጋር ነው ዛሬ እነለማ እየተፋለሙ ያሉት፡፡

መከላከያውንም ሆነ ሌሎች ሰዎችን ወደነለማ ቡደን እንዲቀላቀሉ አስፈላጊ በሆነው ሁሉ የየራሳችንን ጥረትና ድጋፍ ማድርግ እንኳን ሳንችል ሁሉንም ለማ እንጀራ ጋግሮ እንዲሰጥን እንፈልጋለን፡፡ ይባስ ለለማ ቡድን ሸክም እየሆነ ያለው ዲያስፖራ የተባለ ጄሌና በዲያስፖራ የሚደገፉ ተቋማት ናቸው፡፡ እስኪ ግንቦት **7** እየተባለ ሲጨፈርለት የኖረው ቡድን የት አለ**?** ከኦፌኮ በቀርስ አገር ቤት አንድ ቡድን እነኳን እስኪ ትንፍሽ ያለ ማን ነው? ዛሬ ጉዳዩ ን ሁሉ የኦሮሞ ሊያደርጉት እየሞከሩ ነው፡፡ ነገሩ ይገባናል፡፡ አሁንም በሕዝቦ ች መካከል የተፈጠረውን አንድነት ለማ ጣጠል ነው፡፡ ኦፌኮ የኦሮሞ ድርጅት ስለሆነ አደልም መግለጫ ያወጣው፡፡ መግለጫውም እንደዚያ የሚል እንድም ቃል የለውም፡፡ ጥሪው ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ነው፡፡ ስለ በዓዴንና ኦሕዴድ ለጠ/ሚኒ ስቴ ርነት ፉክክርና መከዳዳት ብዙ ወሬዎች አሉ ፡፡ ሲጀምር በዓዴን ውስጥ የነበሩ ወያኔዎች አሁንም ወያኔ ሆነው ኦፒ ዲኦን ሳይሆን ሕዝብን በመክዳት ነው ጦርነት የከፈቱት፡፡ እነ ለማ ድሮስ እነ ደመቀ መኮንንን የእኛ ደጋፊ ይሆናሉ ብለው ነበር? እኛ ከምንለው በላይ አብጠርጥረው ያውቋቸዋል፡፡ ከበዓዴን ወጣት የክልል ወኪሎችና ገዱ ከአልሆነ በቀር አብዛኛው የወያኔ ወኪል ነው፡፡ የተደረገውም ሕዝዊ ሕብረት በእነለማና በእነዚህ የበዓዴን የክልል ወጣት አባላት ነው፡፡ ይህ ሂደት ሕዝቡን ሁለተኛ በማይሸወድበት መልኩ ወደ እንድነት አምጥተውታል፡፡ ይህ በራሱ ትልቅ ድል ነው፡፡ እስኪ ሌላው የሰራው ምን አለ**?** ጭራሽ እንዲህ ያሉ ታላላቅ ድሎችን የሚያጠለሽ በለማና በገዱም ላይ ጥርጣሬ እንዲኖር መርዝ ሲረጭ የከረመ አደለም እንዴ**?** ዛሬ ደርሶ የለማን ቡድን እንዲህ ማድረግ አለበት እያለ መካሪ ሊሆን የሚሞክረው ሁሉ ለማ ያን ሁሉ ሲያደርግ መቼ ሊያምን ፈለገ፡፡ እኔ እንደውም የለማ ቡድን በተለይ በፓርላማ ደረጃ ይሄን ያህል ይበዛል ብዬ አልገመትኩ ም፡፡ አውቃለሁ በዞ ንና ወረዳ ያሉ ብዙዎች ከለማ ጎን ናቸው፡፡ ይህ ማለት ግን ጥቅም ቢያገኝ ከለማ ጋር የሚጸና ትንሽ እንደሆነ በማሰብ ነው፡፡ በዛው ልክ ግን ዛሬ ሚሊየን ለማዎች ስለተወለዱ የለማን ቡድን ማሸነፍ አይቻልም፡፡ የለማ ቡድን በሀ ሳብ ሁሉን ያስማማ በጥቂ ት ጊዜ ሚሊዮኖችን ያፈራ ነው፡፡ ዛሬ ሚሊየን ለማ ነው ያለው

የለማ ቡድን እየ ታገለው ያለው ወያኔ ብቻ አደለም ከወያኔ ፕሮፓጋንዳ አናፋሹ እስከ ኢትዮጵያን አፈርሳለው ብሎ ሲዝትብን እስከነበረው ቡድን ከውኽ ምብር ፈጣሪው እስከ ግልጽ ሴረኛው ነው፡፡ እነ ለማ እንድነትና ኢትዮጵያዊነትን በይፋ እያወጁ በአለበት በአሁኑ ወቅት በአንድነት ሥም የኦነግና የኢትዮጵያን ባንዲራ ይዘው ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት ሌላ ሴራ ሲያሴሩ ይሄው አሁን እኮ እያየን ነው፡፡ ለመሆኑ ለምን ይህን ማረግ አስፈለገ? ለማ የኦነግ ባንዲራ በኦሮሚያ ማንም ይዞ እንዳይገኝ ተናገሮ ሕዝቡን ሁሉ አስትቶት በአለበት በአሁኑ ወቅት የኦነግን ባንዲራ ይዘው በተቃዋሚ ሥም ተሰልፈው ይሄው ሰሞኑን አይተናል፡፡ ግልጽ እንነጋገር፡፡ ኦነግ ከወያኔ ያልተናነሰ ጠላታችን ነው፡፡ ኦነግና ወያኔ አብረው የጠነሰሱት ሴራ ነው ዛሬ ሕዝብ እየማቀቀበት ያለው፡፡ ብዙ ሕዝብ በኦነግ አልቋል፡፡ ኦነግ ሌሎችን በኦሮሞ ሥም በመፍጀት የኦሮሞን ሕዝብ በሌሎች እንደ ጠላት እንዲቆጠር አድርጓል፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ የሕዝብ ልጆ ች በኦነግ ሥም ከዚህች ምድር እንዲጠፉ ተደርጓል፡፡ በኦነግ ሥም ልጁን ወይም አንድ ዘመዱን ያላጣ የኦሮሞ

ቤተሰብ ሥንት እንደሆነ አላወቅም። ኦነግና ወያኔ እኮ ናቸው በሕዝብ መካከል ዘላቂ ሕብረት እንዳይኖር ሥራዬ ብለው ሲሸርቡ የነበሩ። ዛሬ ሕዝብ ያ ሁሉ እውነት ተገልጾለት አንድ ሊሆን እየታገለ ያለውን ትግል እኮ ነው ወያኔ ጦርነት የከፈተችበት። በዚህ ሂደት ውስጥ ኦነግ እድሉን ሊጠቀምና የሴራ ወዳጁን ወያኔን ሊቧደን እያደባ ያለው። እንዲህ በዚህ ወቅት ቁርጠኛ ኢትዮጵያዊነት በተፈለገበትና ሕዝብ ከመቼውም በላይ ኢጋር በፈለገበት ወቅት ዛሬም ለማሴር እንተሻሻለን። ከአሁን በኋላ አካፋን አካፋ ዶማን ዶማ እያልን ካላጠራንው ሊለቀን አልቻለም።

ዛሬ በቦራን የብዙ ወገን ነብስ ጠፍቷል። የተከፈተብን ግልጽ ጦርነት ነው። ጦርነቱን ደግሞ የከፈተው ወሮበላ ወንበዴ መሆኑ ነገሩ የከፋ ሆኗል። አስተሳሰባችን በ 27 ዓመት የወያኔ መርዝ ስለላሸቀ ኦሮሞ ሲሞት ሌላው ከዘፈን ያልተናነሰ ዲስኩር ይነዛል፣ አማራ ሲሞት ሌላው እንደዚህ። የኦሮሞ ደም ደማችን ነው፣ የአማራ ደም ደማችን ነው እያሉ እንመቀለድ አደለም። ቃሉን መጀመሪያ ከልባቸው አውጥተው የተጠቀመበት ጎንደሬዎች ዛሬ የማንም ዘረኛ እንሚያስመስልበት አደለም። አሁን እየሆነ ያለው ጎንደርና ኦሮሚያ በሙሉ ላይ ነው ጦርነቱ ያነጣጠረው። ቀጥሎ ወደሌላው መምጣቱ ለወያኔ የሚቀል መስሏት። ግን አይሳካም። 27 ዓመት የጣለውን ኢትዮጵያዊነት ዛሬ አምጣው ማለት አይቻልም። ግን ኢትዮጵያዊነት ዛሬ እጅግ ተፈልጓል።

ዛሬ የኦሮሚያ ፖሊስ በግልጽ ከሕዝብ ጎን እንደሆነ ስለታማ የጦርነቱ ኢላማ ሆኗል። የአማራም አይቀርልህም። ይልቅ በጥምር ተዋጋ። መሣሪያህን አንሳ። ምድረ ዲያስፖራ በውስጥ ሆነው ትልቅ ተጋድሎ እያደረጉ ያሉ ወገኖችን የሚያጥላላ ሴራ ለሚነዙልህ ጆሮህንና ልብህን ከፍተህ ከምትውል ትኩረትህን ለሕዝብ በማድረግ ለይተህ ከውስጥ ያሉትን ደግፍ። እንደ ግንቦት 7 ና ኦነግ እንዲሁም መሰሎቻቸውን ደጋፊ በመሆን ራስህ የባዘንከው ሳያንስ የሕዝብን ትግል እንቅፋት አትሁን። ዛሬ ግንቦት 7 በሉት ኦነግ ኢጋጣሚን ለመጠቀም አድብተው ያሉ የሕዝብ ጠንቀኛ ጠላቶች እንጂ አንድም ቦታ ከሕዝብ ጋር የሆነ እንቅስቃሴ የላቸውም። ሌላው አስገራሚው ኦነጋውያን በሌላ ድምጻቸው የኦሮሞን ትግል እየመራንው ያለንው እኛ ነን ይሉናል። ሳያፍሩም ፓርላማ የተቃወሙትም በእኛ ግፊት ነው ብለውናል። እንዲህ ባሉ ወሬዎች የባዘነ ሕዝብ ለወያኔ ይፈለጋል ትኩረት ሰጥቶ የሕዝብን ትግል እንዳይቀላቀል።

ኢትዮጵያዊ ነኝ የምትል ሁሉ ወያኔን እየተፋለመ ያለው የለማና ገዱ እንዲሁም አንዳንድ ሌሎች ክልል ጥቂት ቡድኖች እንጂ አንድም በውጭ ያለ ቡድን የለም። ወያኔ ግ 7 ምናምን አሸባሪ የምትለው ህዝብን በግንቦት 7 ሥም ለመግደል እንጂ ግንቦት 7 የተባለ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሌለ ታውቃለች ብቻም ሳይሆን ግንቦት 7 እንዴት መንቀሳቀስ እንዳለበት ቤት ሥራም የምትሰጠው ነች። ኦነግ ለዘመናት በዚሁ መልክ ለወያኔ ሲያገለግል ኖሯል። ብዙ ኦሮሞ በኦነግ ሥም ታርዷል። ዛሬም ገንፍሎ የወጣውን የሕዝብ ትግል ከኦነግ ጋር አያይዛ አረመኔያዊ ድርጊቷን ለመፈጸም ብዙ እየሞከረች ነው። ሆኖም እነለማና ቡድኑ በግልጽ ኦነግ የሚባል የለም አያ ጅቦ ሳታማህኝ ብላኝ ነው ስላሏት ምን እንደምታደርግ ስላጣች ነው። እንደገና አስቸኳ ጊዜ አዋጅ ብላ ያወጣችው።

ከተቃዋሚ ከሕዝብ ጎን ሆኖ በግልጽ እየተጋደለ ያለ ብቸኛ ተቃዋሚ የአፌኮ ቡድን ብቻ ነው። ሰማያዊ፣ መድረክ ምናምን የምትሉት ሁሉ ሁኔታዎችን በማየት ከአደላበት ማደርን ነው እንደ ለሕዝብ ታጋይነት እንዲቆጠርላቸው የመረጡት። የሰማያዊ መሪ ተብዬው ዛሬ ሌላ ቡድን አቋቁሞ ይሄው እንዲጸድቅለት ተፈቅዶለታል። ልብ በሉ ሰማያዊ ውስጥ ብዙዎች በእርግጥም መስሏቸው ተቀላቅለውት ነበር። በመሪነት ግን የወያኔ ሴረኞች ነበሩ። እንዲህ ያሉ ቡድኖችን ወያኔ የምትፈልጋቸው ጥንካራ ሰዎችን የምታጠምድበት ነው። ብዙዎቹ የሰማያዊ ጠንካራ ሰዎች ታስረዋል ወይ ተባረዋል፣ ወይም ተገድለዋል። መሪዎቹ ግን ከዛ ወጥተው ደግሞ ሌላ ቁማር ጀምረዋል። እባብ ሞኝን ሁለት ጊዜ

ነደፈው ይባላል እኛ ግን እስከ መቼ ነው ስንነደፍ የምንኖረው፡፡ መረራን ከዚህ በፊት ብዙ ድርጅት ሞክሮ ወስጥ አድርባዮች እንዲሰገሰጉ በማድረግ አፍርሰውብታል፡፡ አሁን ያለው የመረራ ቡድን (ኦፌኮ) ግን ለወያኔ የሚታጠፍ አደለም፡፡ ከመረራም በላይ ጠንካሮች የተሰበሰቡበት ነው፡፡ ወያኔን እጅግ እያስፈራት ያለው አንዱ ይሄ ቡድን ነው፡፡

አሁን በሕዝባችን ላይ ጦርነት ታወጇል፣ በዛው ልክ ሕዝብ እያመረረ ነው፡፡ ቀጥሎ የሚሆነው እርምጃ በቀጥታ የወያኔ ባለሥልጣናትንና ሆድ አደሮችን ኢላማ ያደረገ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የወሮበላው ቡድን በዋናነት መሪዎች የታሪካዊ ጠላታችን የፋሽት ባንዳ ልጆች ስብስብ እንደሆነ በደንብ እናስተውለው፡፡ የታጠቃችሁ የሕዝብ ልጆች ሁሉ ሕዝብ የክብር ጥሪ እያቀረበላችሁ ነው፡፡ ይህን እድል መቼም አታገኙትም፡፡

ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይታደግ! አሜን!

ሰርፀ ደስታ